664
ለ13

ዳ2ፘ

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
# CUSTOMS COMMISSION

ቀን ... 0 8 2012
Date

ቁጥር 6/0198/12
Ref.No.

**የጉምሩክ ስነ-ስርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ**

**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- የቀረጥ ነፃ የመፍቀድ ስልጣን ስለማሳወቅ፤

የጉምሩክ አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ በገቢ ዕቃዎች ላይ የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጠው በሚኒስቴር መ/ቤቱ በመሆኑ በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎቱን እየጠየቁ በመሆኑ የሚስተናገዱበት የአሰራር ሥርዓት እንዲመቻች ኤጀንሲው በቁጥር በ4/978 በቀን 16/3/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ በጠየቁት መሠረት በኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁ ማኅበራት የሚያስመጧቸው ዕቃዎች እና መሣሪያዎች በተመለከተ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንቡ መሠረት ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚቀርቡ የማበረታቻ ጥያቄዎችን ተቀብለው እንዲፈቅዱ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደሮች ኢንቨስትመንት ቢሮዎች በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/165 በቀን 28/2/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ ውክልና የተሰጠ መሆኑን በመግለፅ፤ ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጡ ማበረታቻዎችና ማበረታቻዎቹ ተፈፃሚ የሚደረጉበትን የአሰራር ሥርዓት የሚወስንና አሁን የሚሰራበትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ደንብ የሚተካ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በሥራ ላይ እስኪውል እና እንደአስፈላጊነቱ ደንቡን የሚያስፈፅሙ መመሪያዎች እስኪወጡ ድረስ የክልል እና የከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮዎች በኢንቨስትመንት አዋጅ በተሰጣቸው የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥልጣን ክልል ሥር ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የማበረታቻ ጥያቄዎችን ተቀብለው በሥራ ላይ ባለው ደንብ እና መመሪያዎች መሠረት ብቁ ለሆኑ ባለሀብቶች ማበረታቻ እንዲፈቅዱ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተወከሉ በመሆኑ የማኅበራቱ ጥያቄ በከተማ እና በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ተደግፈው ሲቀርቡ እንዲስተናገዱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ገንዘብ ሚኒስቴር በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/249 በቀን 1/4/2012 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል፡፡

በመሆኑም የህብረት ስራ ማህበራት ወደ አገር ውስጥ ለሚያስገቡት ዕቃ በከተማና ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች በኩል ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆነው እንዲስተናገዱ እየተፈቀደ ሲቀርብ የጉምሩክ አገልግሎት እንዲሰጥ እያሳሰብኩ፤ ለአፈፃፀም ይረዳችሁ ዘንድ ከድርጅቱ የተላከውን ደብዳቤ 1 ገጽ ኮፒ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ/

- ለጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጽ/ቤት /ያለ አባሪ/
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ /ያለ አባሪ/
- ለዕቃ አወጣጥ አሰራርና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት /ያለ አባሪ/
  ጉምሩክ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህብረት ስራ ኤጀንሲ /ያለ አባሪ/
  አዲስ አበባ

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19

✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ገንዘብ ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance

ቁጥር
Ref.No. ቀ/ነ/ተ/14/249
ቀን
Date 01/04/2012

ለጉምሩክ ኮሚሽን
<u>አዲስ አበባ</u>

የተደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት በኅብረት ሥራ አዋጅ እና ኢንቨስትመንት አዋጅ መሠረት ወደ አገር የሚያስገቧቸውን ዕቃዎች እና ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነፃ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኅብረት ሥራ ኤጀንሲ እየፈቀደ ለጉምሩክ ኮሚሽን ሲፅፍ እንደቆየ በመጥቀስ የጉምሩክ አዋጅን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ በገቢ ዕቃዎች ላይ የቀረጥ ነፃ መብት የሚሰጠው በመ/ቤታችን በመሆኑን በርካታ የኅብረት ሥራ ማህበራት አገልግሎቱን እየጠየቁ በመሆኑ የሚስተናገዱበት የአሰራር ሥርዓት እንዲመቻች ኤጀንሲው በ16/03/2012 በቁጥር በ4/978 በተፃፈ ደብዳቤ፣ እንዲሁም በቤንች ማጂ ዞን አንድነት የገበሬዎች ሁለገብ ኃ.የተ.ኅ.ሥራ ዩኒየን ሁለት Toyota Land Cruiser Pick Up Double Cabin 2020 Mode /3F/ ያስመጣ መሆኑን ገልፆ ከቀረጥ ነፃ ማስገባት እንዲችል በመ/ቤታችን በኩል አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግለት በ25/02/2012 በቁጥር በ4/851 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡

በኅብረት ሥራ ማህበራት የተደራጁ ማኅበራት የሚያስመጧቸው ዕቃዎች እና መሣሪያዎች በተመለከተ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንቡ መሠረት ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ የሚቀርቡ የማበረታቻ ጥያቄዎችን ተቀብለው እንዲፈቅዱ ለክልል እና ለከተማ አስተዳደሮች ኢንቨስትመንት ቢሮዎች በ28/02/2012 በቁጥር ቀ/ነ/ተ/14/165 በተፃፈ ደብዳቤ ውክልና የተሰጠ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ስለዚህ ለኢንቨስትመንት ስለሚሰጡ ማበረታቻዎችና ማበረታቻዎቹ ተፈፃሚ የሚደረጉበትን የአሰራር ሥርዓት የሚወስንና አሁን የሚሰራበትን የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ደንብ የሚተካ ደንብ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ፀድቆ በሥራ ላይ እስኪውል እና እንደአስፈላጊነቱ ደንቡን የሚያስፈፅሙ መመሪያዎች እስኪወጡ ድረስ የክልል እና የከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንት ቢሮዎች በኢንቨስትመንት አዋጅ በተሰጣቸው የኢንቨስትመንት አስተዳደር ሥልጣን ክልል ሥር ለሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች የማበረታቻ ጥያቄዎችን ተቀብለው በሥራ ላይ ባለው ደንብ እና መመሪያዎች መሠረት ብቁ ለሆኑ ባለሀብቶች ማበረታቻ እንዲፈቅዱ በመ/ቤታችን የተወከሉ በመሆኑ የማኅበራቱ ጥያቄ በከተማ እና በክልል ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ተደግፈው ሲቀርቡ እንዲስተናገዱ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ለኅብረት ሥራ ኤጀንሲ
<u>አዲስ አበባ</u>

Lerrer/Tw/

ስልክ Tel 251- 11- 155 24 00,22 66 98
251- 11- 155 00 81,83 86 89
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
አባክዎን መልስ ሲፅፉልን የኛን ቁጥር ይጥቀሱ
ፋክስ Fax 251-11-156 01 24,55 14 96
251-11-155 11 38
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa-Ethiopia